**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ጥር 11 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**በደቡብ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች ወያኔ ባስነሳው ግጭት በርካታ ሰዎች ሞቱ፣ ቤት ንብረታቸው ወደመ፣ ህዝቡም ለስደት ተዳረገ፣ በጅማና አጋሮም ከፍተኛ እልቂት ለ ማድረስ የወያኔ ካድሬዎች በስብቅ እየሰሩ መሆኑ ተጋለጠ፣ የወያኔው ባለስልጣን አዲ ሱ ለገሰ ፓፔረስ የሚባል ሆቴል በባህርዳር ከፍቶ እያስነገደ ነው፣ ሌላው የሕወሓት ባ ለስልጣንም ኢትዮ-ስታር የተሰኘ ሆቴል መክፈቱ ታወቀ፣ ለአባ ገብረመድህን የ40 ሺ ህ ብር ኬክ ተጋገረላቸው፣ ለገበያ ማረጋጊያ ተብሎ በየመጋዘኑ የተከማቸው የነቀዘ ስ ንዴ በእነ ሕላዊ ዮሴፍ ትዕዛዝ ለወጣት ፎረም አባላት በነፃ ተሰጠ»»»»»»»»»»»»**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ**

ወያኔ ለዘመናት ተከባብሮና ተወድዶ የኖረውን ሕዝብ እርስ በእርስ እያጋጨ የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም የጀመረውን ሥልት ቀጥሎበት እንደሚገኝ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ገለፁ::

በደቡብ ክልል ውስጥ በደራሼ ልዩ ወረዳ እና በደቡብ ኦሞ ዞን በጅንካ ወረዳ ውስጥ እርስ በእርስ በተነሳ ግጭት በርካታ ዜጐች ለሞት የተዳረጉ ሲሆን በርካቶች ደግሞ ለከፍተኛ ጉዳት መዳረጋቸውን ይኸው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::

በደራሼ ልዩ ወረዳ ውስጥ ጥር 1 ቀን 2000 ዓ.ም በደራሼ እና በኮምሶ ብሔረሰቦች መካከል በተከሰተ የይገባኛል ጥያቄ በተነሳ ግጭት አምስት ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ ሁለት ፖሊሶችም መገደላቸውን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተለይም የኮምሶ ብሔረሰብ የሕዝብ ብዛ ችን ከፍተኛ ስለሆነ የራሳችንን ወረዳ መመስረት አለብን የሚል ጥያቄ በማንሳት ለዚህ ደግሞ ደራሼዎች ድጋፍ አድርጉልን በማለት ባነሱት ግጭት ሁለት ፖሊሶችን ጨምሮ 7 ሰዎች ለሞት እንደተዳረጉ ታውቋል::

ጥቂት የወያኔ ካድሬዎች በዘረጉት የእርስ በእርስ ማጋጨት ተንኮል ተታልለው የተጠለፉት የኮምሶ ብሔር ተወላጆች በደራሼ ብሔር ተወላጆች ላይ በወሰዱት እርምጃ የፌዴራል ፖሊስንና የወረዳው ፖሊስን ጨምሮ 7 ሰዎችን ለሞት እንደዳረጓቸው በርካታ ሰዎችም አካባቢውን ለቀው እንዲሰደዱ ማድረጋቸውን ከአካባቢው የደረሰን ዘገባ አስረድቶ በሁለቱ ብሔረሰብ መካከል ግጭት እንዲነሳ ሆን ብለው የሰሩት የወያኔ ካድሬዎች ከመሆናቸውም በላይ ግጭቱን በአጭሩ መቅጨት እየቻሉ ሆን ብለው ከዳር ሆነው ይመለከቱ እንደነበርና ሁኔታው እየሰፋ ወደራሳቸው ላይ ሊደርስ መቃረቡን ሲያውቁ የወረዳውንና የፌዴራል ፖሊስ ልከው ሊቆጣጠሩ እንደቻሉም አብራርቷል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደቡብ ክልል የፖሊስ ኮሚሽነር ሆኖ የተሾመው የትግራዩ ተወላጅ የሕወሓቱ ሰው ገ/ኪሮስ ሞገስ የተባለው ግለሰብ ሲሆን ለዚህ ግለሰብ ግጭቱ ሊከሰት ይችላል ስለዚህ አጣዳፊ እርምጃ ይወሰድ ተብሎ የአካባቢው ነዋሪዎች ቀድመው ቢያሳያውቁም ፊቱንም ግጭቱ እንዲቀሰቀስ ያደረጉት እራሳቸው ወያኔዎች በመሆናቸው እልቂቱ እስኪከሰት እያዩ እንደነበርም ይኸው ዘገባ አስረድቷል::

በአሁን ሰዓት የአዋሳ እስር ቤቶች በዚህ ግጭት የተነሳ ታፍሰው በመጡ የደራሼ ወረዳ ነዋሪዎች የተጥለቀለቀች መሆኑንም ጨምሮ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::

በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ ኦሞ ዞን በጅንካ ወረዳ ውስጥ በኮንሶ እና ቦዲ በተባሉት ሁለት ብሔሮች መካከል በተከሰተ ግጭት ከ20 ሰው በላይ ለሞት እንደተዳረጉና በርካቶች ቆስለው በየጤና ጣቢያው ተኝተው እንደሚገኙ ከአካባቢው የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

ታህሳስ 28 ቀን 2000 ዓ.ም ፀቡ የተከሰተው የቦዲ ብሔር ተወላጆች «ያለንበት ቦታ የኛ በመሆኑ አካባቢውን ለቃችሁ ውጡ» በማለት በመሣሪያና በቆንጨራ እንዲሁም በሌሎችም መሰል መሣሪያዎች በመታገዝ ከ20 በላይ የኮንሶ ብሔር ተወላጆችን የገደሏቸው ሲሆን መጀመሪያ ይህን የመሰለ ጥያቄ እንዲያነሱና እልቂቱም እንዲከሰት አንድ የወያኔ ካድሬ በቦታው ተገኝቶ ቅስቀሳ አድርጎ በሄደ በሳምንቱ መሆኑንም ይኸው ዘገባ አጋልጧል::

እራሳቸው ለኩሰው እርስ በእርስ እያጫረሱ መልሰው እነሱው አሳሪ በመሆን ሕዝቡን እያንገላቱት ከመሆኑም ባሻገር በአሁን ሰዓት በጅንካ የሚገኙ መጋዘኖች በእስረኛ ተጣብበው እንደሚገኙ ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል::

ወያኔ ለራሱ አገዛዝ እንዲያመቸው በማሰብ ሕዝቡን እርስ በእርስ እያጋጨና እያጫረሰ ጉዳዩን ከማብረድ ይልቅ እያባበሰ ለዘመናት ተዋልዶ የኖረውን ሕዝብ ማጨፋጨፉ ከደደቢት በረሀ ጀምሮ የተነሳለት አላማ መሆኑን ብንሰማም አሁን ግን በተግባር አየነው ሲሉ የጅንካ ከተማ ነዋሪ አንድ የአባት ጡረተኛ ገልፀዋል::

በጅንካ ከተማ በዞኑ አንድ የግለሰብ ነዳጅ ማደያ ያለ ቢሆንም በማደያው አዛዦቹ የወረዳው ካድሬዎች እንደሆኑና በአካባቢው በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የነደጅ አቅርቦት ለማግኘት እንደተቸገሩና እየተሰቃዩ እንደሚገኙም የደረሰን ዘገባ ገልፆ የአካባቢው ተወላጅ ባለሃብቶች በራሳቸው በጎ ፈቃድ በአካባቢው ሕንፃዎች ለማስገንባት ስራ የጀመሩ ቢሆንም በወያኔ ካድሬዎች በሚደርስባቸው ወከባና እንግልት የተነሳ ስራቸውን እያቆሙ አካባቢውን እየለቀቁ ሲሆን የጅንካ ከተማና አካባቢዋ ነዋሪዎችም ጋዝ እንዳይሸጥላቸው በካድሬዎቹ ስለተከለከሉ በችግር ላይ እንደሚገኝ ኙም ለማወቅ ተችሏል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በጅማና በአጋሮ አካባቢዎች ለብዙ ዘመናት አብረው የኖሩትን የእስልምና እምነት እና የክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ግጭት እንዲፈጠር ሆን ብሎ እየሰራ ያለው ወያኔ በ1999 ዓም በለኮሰው ክብሪት አማካኝነት በርካታ ዜጎች ለህልፈት የተዳረጉ ሲሆን፣ ዘንድሮም በተመሳሳይ መልኩ ጊዜውን ጠብቆ እልቂቱን በሁለቱ የእምነት ተከታዮች መካከል እንዲከሰት ከፍተኛ ስራ በካድሬዎቹ አማካኝነት ውስጥ ለውስጥ እየሰራ መሆኑን ከአካባቢው የደረሰን ዜና አጋልጧል።

ወያኔ ከሕዝቡ በደረሰበት ከፍተኛ ተቃውሞ እንዲሁም አለም አቀፍ ጫናዎች የተነሳ ግራ የተጋባ በመሆኑ በውስጥ ያለውን ጫና ለመቅረፍ ሲል ብቻ ለዘመናት ተዋድደውና ተዋልደው የእምነት ልዩነት በማይታይበት ሐገር ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን የመሰለ አሳፋሪና እጅግ ሰቅጣጭ የሆነ ድርጊት እንዲፈፀም በአሁኑ ሰዓት ውስጥ ለውስጥ እየተጓዘ በመስራት ላይ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በዚህ ደካማ የወያኔ ስልት ተጉዘው ሕዝብን ከሕዝብ ለማናቆር እየተሯሯጡ ያሉት ካድሬዎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡም የአካባቢው የሐገር ሽማግሌዎች ጥሪ ማስተላለፋቸውን የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

ወያኔ ለ16 ዓመት በመከፋፈልና በማበጣበጥ ስልቱ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም በዘንድሮው ዓመት አዲስ የከፋፍለህ ግዛ ስልት ባወጣው መሠረት በቦረና፣ በደራሼ፣ በጅንካ፣ በጅማና በአጋሮ ከተሞች (ወረዳዎች) እያበጣበጠ የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም እየጣረ ሲሆን በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መካከልም ከፍተኛ ክፍተት እየፈጠረ እንዳለ የሰሞኑ ድርጊት አመላካች መሆኑን አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ገለፁ።

እኚሁ የፖለቲካ ተንታኝ እንዳሉት ከሆነ ዛሬ በዩኒቨርስቲው ውስጥ የአካዳሚክ ነፃነት የሌለ በመሆኑ፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት ደካማ ነው በመሆኑና ከዚህም ባሻገር ተማሪዎቹን በዘር ላይ በተመረኮዘ ሁኔታ እርስ በእርስ እንዲጋጩ እየተደረገ ይገኛል። ይህ ደግሞ የወያኔ ቀንደኛ ካድሬዎች እየሰሩት ያለው የቤት ስራ መሆኑን ተማሪዎቹ ቆም ብለው ሊያስቡበት የሚገባ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በተለይም በአርባ ምንጭና በጅማ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ተማሪዎች እርስ በእርስ ተጋጭተው የተጎዱ ተማሪዎች ያሉ ሲሆን በርካታ ተማሪዎችም ለእስር እንደተዳረጉ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል። በአሁን ሰዓትም የአርባ ምንጭና የጅማ ዩኒቨርስቲዎች ትምህርታቸውን ያቆሙ ሲሆን፣ በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ውስጥም ችግሩ ይከሰታል ተብሎ በቋፍ ላይ ያለ መሆኑን ከአካባቢው የደረሰን ዘገባ ገልፆ የባህርዳር ዩኒቨርስቲና ተማሪዎች እርስ በእርስ ግጭት እንዲያነሱ በካድሬ መምህራኑ በኩል ግፊት እየተደረገባቸው መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልጿል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ወያኔ በተለይ በዘንድሮው ዓመት እንደ አዲስ ስልት እየተጠቀመበት ያለው በካድሬዎቹ ውስጥ ለውስጥ ቅስቅሳ ካደረገ በኋላ በብሔርና ብሔረሰቦች እንዲሁም በጐሳዎች መካከል ግጭት እንዲከሰት አድርጐ በሕዝቦች መካከል በሚነደው እሳት እዳር ሆኖ መሞቅ ስራዬ ብሎ ተያይዞታል::

በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልል ሕዝቦችን እርስ በእርስ እያጋጩ በሕዝብ እልቂት እየተደሰቱ ያሉት የወያኔ መሪ መለስን ጨምሮ ቱባ ቱባ ሹማምንቶች ሐገሪቱን ለምድረ በዳነት ዳርገው ሕዝቦቿን በተልካሻ ምክንያት እያጫረሱ አሁን ባሉበት የፖለቲካ አረንቋ ውስጥ ገብተው እየዳከሩ መገኘታቸውን ለ16 ዓመታት ሌት ተቀን ሲሰሩ የነበሩት የቤት ስራ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም አሁንም በዚሁ ሰይጣናዊ ድርጊታቸው ገፍተውበት መገኘታቸው በእጅጉ አሳፋሪ፣ አሳዛኝና አስነዋሪ ድርጊት መሆኑንም መላው የሀገሪቱ ሕዝቦች እየገለፁ ይገኛሉ::

ታሳህሳስ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በደቡብ ክልል በአማሮ ኬላ ወረዳ ውስጥ የወያኔ ካድሬዎች በጉጂ እና ኮይራ በተባሉ ሁለት ብሔሮች መካከል ግጭት እንዲቀሰቀስ አድርገው ቁጥራቸው ለጊዜው ያልታወቁ ሰዎች የሞቱ ሲሆን ቤት ንብረታቸው እንደወደመና ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬ ለቅቀው መሰደዳቸውን ከአካባቢው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::

በዕለቱ በተከሰተው ግጭት ቁጥራቸው በትክክል አይገለፅ እንጂ ከአምስት ሰዎች በላይ እንደተገደሉና ከ15 የመኖሪያ ቤቶች በላይ ሙሉ በሙሉ እንደወደሙ የደረሰን ዘገባ ገልፆ ይህ ሁሉ እልቂት ሲካሄድ እራሳቸው በለኮሱት ግጭት ዳር ሆነው ሲመለከቱት የነበሩት የወያኔ ካድሬዎች ነገ ከነገ ወዲያ በፈፀሙት ተግባር እና እየፈፀሙ ባሉት ታሪክ ይቅር የማይለው ስራ ተጠያቂ መሆናቸውን አለማወቃቸው የዕውቀት ደሀዎች መሆናቸውንና ነገሮችን ማገናዘብ የተሳናቸው እንደ ባዶ በርሜል ከእነ መለስ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ብቻ ተቀብለው በጩኸት ማስተጋባታቸው አሳዛኝ ከመሆኑም በተጨማሪ ለሆዳቸው እንጂ ለህሊናቸው ማሰብ የተሳናቸው ሰዎች መሆናቸውን ጠንቅቀን ተረድተናል ሲሉ አንድ የአካባቢው ተወላጅ ለተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልፀዋል::

ወያኔ ከውስጥና ከውጭ የደረሰበትን የፖለቲካ ኪሳራ ለመሸፈን ሲል ብቻ ለዘመናት የተዋደደ፣ የተዋለደ፣ የተከባበረ ሕዝብ ርካሽ በሆነ የፖለቲካ ሥራ በርካታ ዜጐች እያለቁና ቤት ንብረታቸው ወድሞ በስደት ላይ ባሉበት በዚህ ወቅት ባለሥልጣናቱ በአንፃሩ የሀገሪቱን ሀብት እያሟጠጡ ከቤተሰቦቻቸው አልፎ ተርፎም በሩቅ ዘመዶቻቸው ታላላቅ ሕንፃዎችን እያስገነቡ ከፍተኛ የገቢ ማስገኛ እያደረጉ መሆኑ ታወቀ::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የወያኔው ቡድን ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆነው አዲሱ ለገሰ ለዚህ ተጠቃሽ አንዱ መሆኑን የጠቀሱት የውስጥ አዋቂ ምንጮች በባህርዳር ከተማ ፓፒረስ የተባለ ትልቅና ዘመናዊ ሆቴል አስገንብቶ ወደ ከተማዋ የገባ ማንኛውም ባለሥልጣን በግዴታ በዚህ ሆቴል እንዲሰተናገድ የሚደረግ መሆኑንም ገልፀዋል።

ከፓፒረስ ሆቴል በተጨማሪ ንብረትነቱ ለጊዜው የማን እንደሆነ ያልታወቀ የሕወሓት ከፍተኛ ባለሥልጣን እንደሆነ የተነገረለት ኢትዮ ስታር የተባለ ሆቴልም በአንዲት የትግራይ ተወላጅ ሴት ስም የሚንቀሳቀስ ሌላው የገንዘብ ማግበስበሻቸው ሲሆን ይህ ሆቴል እንደ አዲሱ ለገሰ ሆቴል ሁሉ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች በዚህ እንዲስተናገዱ የሚገደዱበት መሆኑንም ምንጮቹ ጠቁመው ለምሳሌ ያህል ይህ ተጠቀሰ እንጂ ሁሉም ባለሥልጣናት ሕዝቡን እርስ በእርስ እያፋጁ እነሱ ሀብታቸውን እያጠራቀሙ መሆኑ ከሰው ባህርይ ውጭ ግለኝነት የተጠናወታቸው መሆኑን ምግባራቸው ያስረዳል በማለት ጉዳዩን የሚያውቁት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ያስረዳሉ።

በዚህ በባህርዳር ከተማ የሚገኙት እነዚህ ሁለት የወያኔ ባለሥልጣናት ንብረት ሌሎች ሆቴሎች ተወዳድረው እንዳያሸንፏቸው በግዴታ ለመንግስት ሠራተኛና ለወታደራዊ ባለሥልጣናቱ አስቀድሞ መመሪያ ከመሰጠቱም በላይ ክፍያ የሚከናወነው ከመንግስት ካዝና በቀጥታ ለሆቴሎች መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀው የባህርዳር ከተማ ነዋሪዎች ይህንን በማወቃቸው ሌሎች ተስተናጋጆች ወደ እነዚያ ሆቴሎች እንዳይገቡ በከፍተኛ ሁኔታ ጥረት እያደረጉ መሆኑንም አብራርተዋል።

በቅርቡም ትምህርታቸውን ጨርሰው ያለስራ የተቀመጡትን የባህርዳር ወጣቶች በቡድን ተሰባስባችሁ የኮንዶሚኒየም ቤት መስሪያ ግብአቶችን እንድታቀርቡ በሚል ሰበብ ወጣቱን የወያኔ ደጋፊ ለማድረግ ካድሬዎቹ ለማግባባት ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ወጣቶቹ የማይሞከር ከመሆኑም በላይ የማይታሰብ ነው በማለታቸው ብቻ አፍሰው ለ5 ቀን ያህል እስር ቤት እንደከተቱዋቸው ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልፆ አሁንም የምርጫ ወቅት የደረሰ በመሆኑ የወጣቱን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ብቻ በየአካባቢው ተደራጅታችሁ ሥራ መሥሪያ ገንዘብ እንሰጣችኋለን እያሉ ወጣቱን ለማታለል ቢሞክሩም ተመሳሳይ ምላሽ እየተሰጣቸው መሆኑ የወያኔን ካድሬዎች ናላ እየበጠበጡ መሆኑም ታውቋል።

የወያኔ ባለሥልጣናት ሕዝቡን እርስ በእርስ እያጋጩ፣ ወጣቱን ለስራ አጥነት እየዳረጉት፣ የሀገሪቱን ሀብት እየዘረፉ ይህም አልበቃ ብሏቸው ገበሬውን የመሬት ግብር መክፈል በማይችለው ሁኔታ እየጫኑበት ባለበት በዚህ ወቅት ከተሜውን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በግዴታ መዋጮ እንዲያዋጣ እያስገደዱት መሆኑን ከባሌ ከተማ ሸልኮ የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

በባሌ ሮቤ ከተማ ሰሞኑን የወያኔ ካድሬዎች ሕዝቡ ገንዘብ እንዲያዋጣ ለማግባባት ቢሞክሩም አሻፈረኝ በማለቱ ቤት ለቤት እየዞሩ የሚልሰውና የሚቀምሰው የሌለውን ሕዝብ 20 ብር እና ከዚያም በላይ ሲያስከፍሉ የንግድ መኪና እና የንግድ መደብሮች ያላቸውን ደግሞ ከ500 ብር በላይ በግዴታ እያስከፈሏቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ አጋልጧል::

የወያኔው ቡድን እነ ወዲ ዜናዊ በሕዝብ ላይ የሚሰሩት ግፍና በደል አልበቃ ብሏቸው አሁን ደግሞ ሕዝቡ የዕለት ጉርስ በቸገረው ወቅት ይህን የመሰለ በግድ ክፈሉ የሚል ትዕዛዝ አውጥተው ባሌ ሮቤና ባሌ ጉባ ከተማ ያሉትን ነዋሪዎች እያመሱት መገኘቱ ሀገሪቷን ለምድረበዳነት ሕዝቦቿን ለድህነት ዳርገው ሊሰወሩ ይሆን? እያሉ የሚጠይቁ የሐገሪቱ ዜጐች በርካቶች ናቸው::

እንዲህ ያለ ግፍ በሕዝብ ላይ ወያኔዎች እየፈፀሙ ባለበት ወቅት የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ ያሉት የመለስ ዜናዊ ነፍስ አባት አባ ገ/መድህን ለገና በዓል በላሊበላ ከተማ ተገኝተው ያከብራሉ ተብሎ እየተጠበቁ ባለበት ዕለት አሞኛል በሚል ሰበብ ቀርተው በቅድስት ማርያም ግቢ ውስጥ ባሰሩት ቤተ መንግስት ውስጥ በመሆን ከየደብሩ እንዲመጣላቸው ባዘዙት መሠረት የ40 ሺህ ብር ኬክ እንደተገዛላቸው ምንጮች አጋለጡ::

የመንፈሳዊ አባትነት ቅንጣት ታክል ውስጣቸው የሌለው አባ ገ/መድህን በጥቂት ተከታዮቻቸውና የቤተክህነት አለቆች ጋር በመሆን ለገና በዓል ኬክ ከየደብሩ ገንዘብ ወጪ ተደርጐ ተጋግሮ እንዲቀርብላቸው ባዘዙት መሠረት አዲስ አበባ ከሚገኙ አብያተ ክርስትያናት ሁሉም በየበኩላቸው ይዘው የመጡ ሲሆን ታህሳስ 29 ቀን 2000 ዓ.ም ብቻ የመጣላቸው ኬክ ሲደመር ከ40 ሺህ ብር በላይ ወጪ እንደተደረገበት ምንጮቹ ያጋለጡ ሲሆን፣ አባ ገ/መድህንም በበኩላቸው ለመጡት የደብር አለቆች የሚሆን ጮማና ውስኪ አዘጋጅተው እንደጠበቋቸው ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ሕዝበ ክርስቲያን የገናን ፆም መፍቻ አጥቶ በየቤተክስቲያኑ ደጃፍ ላይ ተኮልኩሎ እያለ የወያኔው መሪ መለስ ነፍስ አባት የሆኑት አባ ገ/መድህን ይህንን በመሰለ አለማዊ ነገር ላይ ተሰማርተው ፍፁም የመንፈሳዊ አባትነት ቅንጣት ታክል በውስጣቸውም ሆነ በድርጊታቸው የሌለ ከመሆኑም ባሻገር ስለሚበሉትና ስለሚቀቡት ሽቶ እየተጨነቁ በምድር ላይ ይህን የመሰለ አሳፋሪና እምነቱን የሚያበላሽ ሥራ የሚሰራ የእምነት አባት መሆናቸው በአለም ላይ የመጀመሪያው አባ ገ/መድህን ሊሆኑ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም ሲሉ ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

በኢትዮጵያዊ አቅም የማይቻለውን የአለም ሀብታሞች የሚያሽከረክሩትን ሐመር መኪና ካልተገዛልኝ ብለው ከየደብሩ ሕዝብ ለካህናትና ለቤተ ክርስቲያናት መደጐሚያ ይሆናል እያሉ የሚያስቀምጠውን ሙዳይ ምፅዋት ከየቤተክርስቲያኑ ተገልብጦ ተወስዶ መኪናው እንዲገዛላቸው የተደረገ ሲሆን፣ እንደ ቀድሞ አምባገነን መሪ መንግስቱ ኃይለማሪያም ፎቷቸው በየአደባባዩ እንዲሰቀል በማስገደድ እጅግ በመቶ ሺዎች በሚቆጠር የሕዝብ ገንዘብ ወጪ ያደረጉ መሆናቸውን የተከታተሉ የዕምነቱ ተከታዮች በሀዘን ለፈጣሪያቸው እኚህን ምግባረ ብልሹ ካድሬ ከቦታው አንሳልን እያለ እያለቀሱ ለአምላካቸው ልመና ሲያቀርቡ ማድመጥ የቀን ተቀን እንቅስቃሴ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የወጣት ፎረም አባል ተብለው በወያኔ ተመልምለው የደህንነት ስራ እየሰሩ ያሉት ወጣቶች ለገበያ ማረጋጊያ ይረዳል ተብሎ በየክፍለ ከተማው የተከማቸው የነቀዘውን ስንዴ ከየመጋዘን እያወጡ ወዳልታወቀ ስፍራ እየወሰዱ መሆኑን የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ፡፡

በተለይም በልደታ ክፍለ ከተማ መጋዘን ውስጥ ለሕዝቡ በየወሩ በኩፖን ይሸጣል ተብሎ የተቀመጠውን የነቀዘ ስንዴ የፎረም አባል ወጣቶቹ ያለአንዳች ችግር በመጋዘን ውስጥ ያለውን ስንዴ በመኪና አጓጉዘው የወሰዱ ሲሆን ለነጋዴም ሸጠው ለሚሰጣቸው ግዳጅ መወጫ ሊያውሉት እንደሚችሉ ምንጮች ግምታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡

በአዲስ አበባ ያሉት ወጣቶች በእነ ሕላዊ ዮሴፍ ተቆጣጣሪነት የሚመሩ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች ወያኔ ከገባበት አጣብቂኝ ውስጥ ለመላቀቅ በማሰብ ብቻ ጥቂት ወጣቶችን በገንዘብ በመደለል የደህንነት ስራ እንዲሰሩለት ለማግባባት የሞከረ ቢሆንም በአሁን ሰዓት ወያኔ ባጋጠመው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር የተነሳ ለወጣቶቹ የሚከፍለው በማጣቱ በየመጋዘን ያለውን የነቀዘ ስንዴ አውጥተው እንዲሸጡና እንዲጠቀሙበት እነ ሕላዊ ዮሴፍ ትዕዛዝ ሳይሰጡዋቸው እንዳልቀረም ምንጮቹ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል፡፡

የወያኔው ቡድን የተማረ ኃይል እንደሚፈራ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በሚያሳየው ድርጊት የታወቀ ሲሆን፣ ሰሞኑን 1500 የግብርና ባለሙያዎች ከስራ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሊያባርር መዘጋጀቱን ከገጠር ግብርናና ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ምንጮቻችን የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ለብዙ ዓመታት በግብርና ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት እነዚሁ የግብርና ባለሙያዎች የኦሮሞና የአማራ ብሔር ተወላጆች የሆኑ ከ1500 በላይ የሚሆኑት በግዴታ የ3 ወር እረፍት እንዲወስዱ ተደርገው ከ3 ወር በኋላ ሲመለሱ የስንብት ደብዳቤ እንዲሰጣቸው በአቶ አዲሱ ለገሰ ፊርማ ትዕዛዝ የተላለፈ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ሰሞኑን ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል::

በአንፃሩ የትግራይ ተወላጅ ሙያው የሌላቸው የሕወሓት አባሎች ለትምህርት ተብለው ወደ ሆላንድና ሌሎችም ሀገሮች እንዲሄዱ አዲሱ ለገሰ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ ለመባረር ከተዘጋጁት ውስጥ በግብርና ሙያ አንቱ የተባለ እውቀት ያካበቱና በሀገሪቱ ጥቂት ከሚባሉት ውስጥ የሚካተቱ እንደሚገኙበት ምንጮቹ ገልፀው እነዚህ የሀገሪቱ የግብርና ባለሙያዎች ከስራ ሊባረሩ የተዘጋጁት የአማራ እና የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች በሆኑትና በፖለቲካ ወገንተኝነት ለተቃዋሚ ያዘነብላሉ ተብሎ ባልተረጋገጠ ነገር ላይ ተመስርቶ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በሌላ በኩል የወያኔው የተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆነው አቶ ክፍሌ ጉደኢ የተባለው ግለሰብ ከምክር ቤት አባልነት እራሱን ማግለሉ ታወቀ:: ጥር 8 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው መደበኛ የተወካዮች ምክር ቤት ተብዬ ስብሰባ ላይ እንደተገለፀው ግለሰቡ አሁን ያለው አካሄድ ስላልጣመኝ በገዛ ፈቃዴ ከፓርቲውም ከምክር ቤት አባልነቴም ለቅቄያለሁ በማለት ለአፈ ጉባኤ ተሾመ ቶጋ ባቀረበው መሰናበቻ ደብዳቤ መሆኑ ታውቋል::

ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ የወያኔ ክንፍ የሆነው የደኢህዴን አባል ሆኖ በተወካዮች ምክር ቤት አባልነት ስርዓቱን ሲያገለግል የቆየ ሲሆን፣ ወያኔ በቅርቡ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በጀመረው የጐሳ ግጭት ሳቢያ በተለይም በደቡብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻልበት ሁኔታ ሕዝቦች እርስ በእርስ እየተጋጩ እና እየሞቱ መፍትሄ ሳንሰጥ ዝም ብለን መቀመጣችን ወንጀለኛ ስለሚያደርገን አሁን ያለው አካሄድ ስላልተስማኝ ከምክር ቤት አባልነቴም ከፓርቲውም እራሴን አግልያለሁ በማለት ባቀረበው መሰናበቻ ደብዳቤ ከጥር 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከምክር ቤት አባልነቱም ሆነ ከፓርቲ አባልነቱ የተወገደ መሆኑን በዕለቱ በነበረው የምክር ቤት ስብሰባ ላይ መገለፁ ታውቋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ወያኔ እያካሄደ ያለው ፖለቲካ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከሰረና ውድቀት እያመጣበት መሆኑን የራሴ የሚላቸው ካድሬዎች በሚወስዱት እርምጃ እያረጋገጠ ሲሆን፣ በተለይም በኦህዴድና በብአዴን ካድሬዎች ዘንድ የሕወሓት የበላይነት መንገስ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ እንዳልተወደደም እየገለፁ ይገኛሉ ያለው ይኸው ዘገባ በአሁን ሰዓት በምክር ቤት አባሎችም ውስጥ የእርስ በእርስ ስምምነት ጠፍቶ የቃላት ጦርነት እየገጠሙ እንደሚገኙም አጋልጠዋል።

በመጨረሻም ባልተገራ አንደበታቸው ሕዝብን እያዋረዱ ያሉት የወያኔ ባለሥልጣናት ይህ አልበቃ ብሎ ሀገሪቱን ለድህነት ሕዝቡዋን ለባርነት ለመዳረግ እያደረጉ ያለው ሙከራ አልሳካ ያላቸው ቢሆንም አሁንም እንደገፉበት ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ሰሞኑን ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ሾልኮ የወጣ ዘገባ እንዳጋለጠው ከሆነ የወያኔው መሰሪ ቡድን በሁሉም መንግስታዊ መስሪያ ቤት ውስጥ የመዋቅር ለውጥ በሚል ለብዙ ዓመታት ከሰሩበት መስሪያ ቤት በርካታ ሰራተኞችን ከስራ የሚያፈናቅል ጥናት እየተደረገ መሆኑንም ዘገባው አጋልጧል።

ሾልኮ እንደደረሰን ዘገባ ከሆነ በሁሉም መንግስታዊ መስሪያ ቤት ውስጥ ጥናቱ ተጠናቆ ያለ ሲሆን፣ በአብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎችና ደጋፊዎች ናቸው የተባሉ የመንግስት ሰራተኞች በመዋቅሩ ውስጥ እንደማይካተቱ ገልፆ ከተባረሩም በኂላ አስፈላጊው የካሣ ክፍያ እንደማይፈፀምላቸው አብራርቷል።

ወያኔ በዘረጋው ዘረኛ ፖለሲ እየተጠቀመ የትግራይ ልጆች ለዕድገትና ለሹመት ሲታጩ የአማራውና የኦሮሞ ብሔሮች ደግሞ ከስራ የማፈናቀል ዕጣ እየደረሰባቸው ለሀዘንና ለትካዜ እየተዳረጉ እንደሚገኙ እየታወቀ በእሳት ላይ ቤንዚን እንዲሉ አሁንም የእስከዛሬው ሳያነስ ሌላ የመንግስት ሰራተኞች መፈናቀል ሊያስከትል የሚችል ዕቅድ መንደፋቸው በጣም የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው ሲሉ አስተያየታቸውን የሚሰጡት በርካታ የመንግስት ሰራተኞች ናቸው።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com